በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰሜን አሜሪካ
ሰንበት ት/ቤቶች አንድነት
The Ethiopia Orthodox Tewahedo Church-North America Sunday Schools Union (EOTC-NASSU)
Tel: (630) 660-1850 ~ Fax: (630) 328-7346 ~ P.O. Box 9544 ~ Naperville, IL 60567
URL: http://www.onetewahedo.org ~ e-mail: info@onetewahedo.com

«እስመ ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ ወሠለስቱ ጉባኤ በስምየ ሀየ እሄሉ አነ ማዕከሎሙ (ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።)» ማቴ ፲፰ ፤ ፳

« ትጉሁ ወቁሙ በሃይማኖት ተዐገሡ ወጽንዑ። ወኩሉ በፍቅር ግበሩ። (ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጎልምሱ ጠንክሩ። ሁሉን በፍቅር አድርጉት።)» ፩ ቆሮ ፲፮ ፲፫

**ቀን መጋቢት ፳፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም**
**ቁጥር** 6/1999

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን**

**ለ______________________________________________**

የተከበራችሁ አባቶች ፤ የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት አባላት እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም ፣ በሕይወትና በጤና ጠብቆ አደረሳችሁ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤውን ብርሃን እንድናይ ስላደረገን ስሙ ከአጽናፈ ዓለም እስከ አጽናፈ ዓለም የተመሰገነ ይሁንልን አሜን ።

ከመንፈሳዊ ሰላምታችን በመቀጠልም የማኅበራችን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከ፮ኛው ዓመታዊ ጉባኤ መዝጊያ ቀን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ያደረገውን የሥራ እንቅስቃሴዎች በአጭር በአጭሩ ከዚህ በታች እንደሚከተለው እናቀርባለን።

- ❖ ማኅበራችን ከማህበረ ቅዱሳን የበጎ አድራጎት ክፍል ጋር በመተባበር የዋሻ አምባ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የወፍጮ ተከላ ፕሮጀክት በሐምሌ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም አስጀምሮ በማስፈጸም ላይ ይገኛል። የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ሂደት ፳፩ ከመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን በቅርቡ ሥራውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይጀምራል። የዚህ ፕሮጀክት ጠቅላላ ወጪ $55225.43 ብር (በኢትዮጵያ)ነው።
- ❖ በጅማ ፣ በኢልባቡርና በምዕራብ ወለጋ በአብያተ ክርስቲያናትና በምእመናን ላይ በአክራሪ እስላሞች ከፍተኛ አደጋ መድረሱን ሁላችንም የምናውቀው ነው። ማኅበራችንም ይህንን አሰቃቂ አደጋ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ባደረገው የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ በቺካጎ ፣ በሳን ሆዜ ፣ በአትላንታ ፣ በቨርጂኒያና በሚኒሶታ ከሚገኙ አባላት $10200 ዶላር ለማሰባሰብ ችሏል። የተሰበሰበውን ገንዘብ በታቀደለት ቦታ ላይ ለማዋል ቅድመ ዝግጅቶች እየተካሄዱና ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመነጋገር ላይ ይገኛል።
- ❖ የዘንድሮ ፯ኛው ዓመታዊ ጉባኤ የሚካሄደው በዴንቨር ኮሎራዶ ውስጥ በሚገኘው በደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢ.ኦ.ተ.ቤተክርስቲያን ውስጥ ***ከነሐሴ ፳፭-፳፯/፲፱፻፺፱ ዓ.ም ወይም ከAugust 31 – September 2, 2007 ነው።*** ለዚህም ጉባኤ ቅድመ ዝግጅቶች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመደረግ ላይ ይገኛሉ።
- ❖ ማኅበራችንም ባሉት የተለያዩ የሥራ ክፍሎቹ አማካኝነት የተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራትን በማካሄድ ላይ ይገኛል። የመዝሙር ክፍላችን ዘንድሮ በሚደረገው ጉባኤ ላይ የሚቀርቡት መዝሙራት ምን መምሰል አለባቸው በማለት የተለያዩ የሰንበት ት/ቤቶች የመዝሙር ክፍል ተጠሪዎች ጋር በመወያየት ላይ ይገኛል። የሥራ ዕቅድና ክንውንና የግንኙነት ክፍሎቻችንም ከተለያዩ የሰንበት ት/ቤቶች ተጠሪዎች ጋር በመገናኘት ለዘንድሮ ጉባኤ የአባላት ተሳትፎ እንዲጨምር ጥረት እንዲያደረጉና

መልእክቱን በአካባቢያቸው ለሚገኙ የሰንበት ት/ቤቶች እንዲያስተላልፉ በተለያዩ ጊዚያት ውይይቶችን በማካሄድና በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ።

ማኅበራችን አቅሙ በፈቀደ መጠን ሁሉ የሚያደርጋቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች እን
ዳሉ ሁሉ በአንጻሩ ደግሞ ለእድገታችን እንቅፋት የሆኑ በርካታ ችግሮች አሉ። ከችግሮቻችን
አንዱ ማኅበራችን ባሉት የሥራ ክፍሎች ውስጥ አባላቶቻችን አለመሳተፍ ነው። ይህንን ችግር
በየዓመቱ በምናደርጋቸው ዓመታዊ ጉባኤዎች ላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። ሁላችንም እን
ደምናውቀው የምንኖርበት ሀገር እንደ ሀገራችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት እጅግ የተመቻቸ
ባይሆንም ነገር ግን ባለን አቅም ሁሉ መንፈሳዊ ግዴታችንን መወጣት አለብን። ሁላችንም
ባለን አቅም ሁሉ ለቤተክርስቲያናችን መስዋዕትነትን መክፍል አለብን። መስዋዕትነትን መክፈል
አለብን ስንል እንደ ዘመነ ሰማዕታት ያለ መስዋዕትነት ብቻ ሳይሆን ዘመኑ በፈቀደልን
በጉልበት ፣ በጊዜ በዕውቀትና በገንዘብ ማለታችን ነው። የቅዱስ ዮሐንስን መልእክት ሁላችን
ም ልናጤነውና ልናስተውለው ይገባናል። « ልጆቼ ሆይ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአን
ደበት አንዋደድ።» ፩ኛ ዮሐንስ ፫ ፤ ፲፰። ሁላችንም ለቤተክርስቲያናችንና ለማኅበራችን ያለን
ን ፍቅርና እድገት የምንገልጸው በሥራ እንጂ በአንደበትና ከንፈርን በመምጠጥ አይደለም።
በተጨማሪም ዛሬ ቤተክርስቲያናችን ከእኛ ከልጆቿ የምትፈልገው ጠንክሮ መስራትን ነው።

የተከበራችሁ አባቶች እንዲሁም የማኅበራችን አባላት ማኅበራችንን አሁን ካለበት ወደ
ተሻለ እድገት ላይ ለማድረስ ሁላችንም ባለን ጸጋ ማኅበራችን ባሉት የሥራ ክፍሎች ውስጥ
በመግባት እንስራ። በዚሁ አጋጣሚ በዌብ ዲዛይን ችሎታ ያላችሁ አባላቶቻችን በሚከተለው
አድራሻ ልታናግሩን ትችላላችሁ። committee@onetewahedo.org.

ባጠቃላይ ስለ ማኅበራችን ያላችሁን አስተያየት ወይም መረጃ ለማግኘት ከፈለጋችሁ
በላይ በተጠቀሰው የኢ-ሜይል አድራሻ ልታገኙን ትችላላችሁ።

የትንሣኤው በዓል የሰላም ፣ የደስታና የፍቅር በዓል ያድርግልን። አምላካችን ሁላችን
ንም በሰላም ጠብቆ ለ፯ኛው ጉባኤ ያድርሰን። አሜን!!!

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ!



ዲያቆን እሥጢፋኖስ ሥዩም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት ዋና ሰብሳቢ።